የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት

# ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ

# DEBUB NEGARIT GAZETA

## OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLES' REGIONAL STATE

13 ዓመት ቁጥር 66/2000
አዋሣ ታህሳስ 14 ቀን 2000

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ

13 Year No 66/2000
Awassa Dec. 24/2007

**በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የአፈጻጸም ደንብ መ□ቢ□**

የክልሉ መንግሥት ለአገራችን ብሎም ለክልላችን ኢኮኖሚ መሠረት ለሆነው ግብርና ልማት መሬት ዋንኛው ግብአት መሆኑን በመገንዘብ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ□ር 110/99 የደነገገ በመሆኑ ፣

ይህን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ወደተግባር ለመተርጐምና በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ደንብ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በገጠር መሬት አጠቃቀም ረገድ የተጣሉ ገደቦችን በዝርዝር በማስቀመጥ ተጠቃሚው መብቱንና ግዴታውን አውቆ ይዞታውን በአግባቡ እንዲጠቀም ለማድረግ፣

አዋጁን ለማስፈጸም እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለማሻሻል ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን በግልጽ ማስቀመጥ ተገቢ በመሆኑ፣

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር ምክር ቤት በአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## □ቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ " የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ ደንብ " ቁ□ር 66/2000 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1. በዚህ ደንብ ውስጥ ያሉት ቃላትና ሐረጐች ሁሉ በአዋጁ ውስጥ ከተሰጣቸው ትርጓሜ ጋር በተጣጣመ መንፈስ ጁተረ□ማሉ፡፡
2. □ዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ ውስጥ

ሀ "አዋጅ" ማለት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግሥት □□□ር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 ማለት ነው፡፡

ለ. "መስተዳድር ምክር ቤት" ማለት የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መስተዳድር ም/ቤት (ካቢኔ)ማለት ነው፡፡

ሐ. "ቢሮ" ማለት የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ማለት ነው፡፡

መ "የገጠር መሬት" ማለት ከማዘጋጃ ቤት ክልል ውጪ ወይም አግባብ ባለው ሕግ ከተማ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ውጪ ያለ ማንኛውም መሬት ማለት ነው፡፡

ሠ. "ኮሚቴ" ማለት በቀበሌ ደረጃ በሕዝብ ተመርጦ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጉዳይን የሚያስፈጽም ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

ረ "□□ል ጁዞ□" ማለት ከመንግሥት ወይም ከግል ይዞታነት ውጭ የሚገኝ እና የአካባቢ ነዋሪዎች በጋራ ይዞታነት የሚጠቀሙበት ሲሆን ለግጦሽ፣ ለደንና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች እየዋለ ያለ መሬት ነው፡፡

ሰ. "□□ራ □ርሻ" ማለት ባለይዞታው ይዞታውን ለሌላ ሰው በመ□ቀ□ ሰብል ማዝራት/ማስተከል ሲሆን ሰብሉ ሲ□ርስ እንደውላቸው ተካፍለው የሚወስዱበት አሰራር ነው፡፡

**The Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State, Rural Land Administration and Use Regulation.**

**Preface**

**Where as, the regional government issued a rural land administration and use proclamation No 110/2007 recognizing land as an important agricultural input and an economic base for the region and the country as whole.**

**Where as, to implement this rural land administration and use proclamation, it becomes necessary to issue regulation.**

**Where as, describing restriction imposed on rural land use right in detail is needed so that the landholder know his rights and obligations and properly manage the land.**

**Where as, to implement and, if necessary, to amend the proclamation, it is needed to state miscellaneous provisions.**

**There fore, the regional administrative council issued this regulation based on the provision of the proclamation No 110/2007 article 18 sub articles 1.**

## Section One

## General

### 1. Short Title

**This regulation shall be cited as the "Rural Land Administration and use regulation" No 66/2007 issued to implement the Proclamation.**

### 2. Definition

1. **All words and phrases written in this regulation should be translated and defined in the same manner as in the proclamation.**
2. **Without the prejudice to this article sub article 1 in this regulation: -**
   - A. **"Proclamation" means the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State Rural Land Administration and Use Proclamation No.110/2007.**
   - B. **"Administrative Council" means the administrative council of Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State.**
   - C. **"Bureau" means the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State Bureau of Agricultural and Rural development.**
   - D. **"Rural Land' means those lands outside the administrative boundary of municipality or any land found outside legalized urban areas / towns/.**
   - E. **"Committee" means publically elected body of local community at Kebele level to carry out land administration and use activities.**
   - F. **"Communal Holding" means the land neither possessed by Government nor privately, practically being used either for grazing or forest or any other social services by the local community.**
   - G. **"Share Cropping" means the way of using land when the land holder allows share cropper to cultivate crop on his holding and share the harvest according to their agreement.**

ሸ. "የመሬት ደረጃ" ማለት የመሬቱን የምር□ማነትና የሌሎች አመቺ ሁኔታዎች ማለት የለምነት ደረጃ፣ የመሠረተ ልማት መስፋፋት፣ የአየር ንብረትና የመሳሰሉትን ታሣቢ.ዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የሚወጣ ደረጃ ማለት ነው፡፡

ቀ. "የእርሻ መሬት" ማለት በዓመታዊ ወይም በቋሚ ሰብል የተሸፈነ መሬት ነው፡፡

በ. "ተዳፋት የእርሻ መሬት" ማለት የመሬቱ ተዳፋትነት ከፍ እያለ በመሄዱ ምክንያት ተገቢ የአፈር ጥበቃ ሥራ ካልተሠራ በስተቀር ለ□ሻ ሥራ የማይፈቀድ መሬት ማለት ነው፡፡

ተ. "□ጹዞ□ ማረ□□□ ደብተር" ማለት ለአንድ አርሶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደርና አርብቶ አደር □ጹም ሌሎች የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች □ጹዞታውን መጠን በመለካትና አዋሳኞች በመመ□□ብ □ሚሥ□ □ጹዞ□ ማረ□□□ ሰነድ ማለት ነው፡፡

ቸ. "የህዝብ ጥቅም" ማለት በመሠረተ ልማት አውታሮች ማለትም በትምህርት፤ በጤና፤ በመንገድ፤ በውኃ---ወዘተ ተቋማት የሚገኝ የህዝብ የጋራ አገልግሎት ማለት ነው፡፡

ኀ. "በከተማ ክልል የሚኖር አርሶ አደር" ማለት ይዞታው በከተማ ክልል ሆኖ በግብርና ሥራ የሚተዳደር አርሶ አደር ማለት ነው፡፡

**3. □□ታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

**4. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ በሚገኝ በማንኛውም ዓይነት የገጠር መሬትና በከተማ ክልል ለግብርና ሥራ በዋለ መሬት ላይ ተ□□ሚ ጹሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ስለማረጋገጥ

5. የገጠር መሬት ስለማግኘትና ስለመጠቀም፡-

1. በግብርና ሥራ መሠማራት የሚፈልጉ የገጠር ወጣቶች፡-

   ሀ/ በፈቃደኝነት በሰፈራ ኘሮግራም ተሳትፈው መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡

   ለ/ ከሚመለከተው አካል የወል ወይም የመንግሥት መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል ፡፡

2. ባልና ሚስት በይዞታቸው እኩል የመጠቀም መብት ያላቸው ሲሆን፡-

   ሀ/ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ይዞታ በጋራ የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

   ለ/ ከጋብቻ በኂላ በውርስ ወይም በሌላ መንገድ ያገኙትን መሬት በጋራ የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

**H. "Land Classification" means a category of rural land based on productivity and other criteria such as fertility status, infrastructure, climate and others.**

**I. "Cultivated Land" means a land covered by either annual or perennial crops.**

**J. "Sloppy farm Land" means a land, not advisable for cultivation unless different conservation techniques are applied as changing in gradient/slope/.**

**K. "Holding certificate" means written document issued to a peasant farmer/s/ or semi pastoralist or pastoralist or any other rural land holder/s/, by measuring and registering the size, neighbors, fertility status, etc of the holding.**

**L. "Public Use" means a common service obtained from infrastructures such as education, health, transport and water…etc..**

**M. "Peasant farmers living in urban territory" a peasant farmer who has holding in urban territory and whose livelihood depends on agriculture.**

### 3. Gender Reference

**The provision of this regulation set for the masculine gender shall also apply to the feminine gender.**

### 4. Scope of the Regulation

**This regulation shall be implemented with in the southern Nations, Nationalities and people regional state in all type of rural land and lands used for agricultural purposes in urban territory.**

## Section Two
## Assuring Rural Land use Right

**5. Rural Land Possession and Use**

**1. Rural Youths who wish to be engaged in Agriculture:-**

**A. Shall have the right to participate voluntarily in settlement program to get and use rural land.**

**B. Shall get and use rural land from communal land government's holding; from competent authority.**

## 2. Husband and wife shall have equal use right on their holding:-

**A. Husband and wife shall jointly use their possession which they got before their marriage.**

**B. Husband and wife shall jointly use the rural land that they got after marriage through inheritance or other means.**

3. ወላጆቻቸውን በማጣት በሞግዚት ከሚያድጉ ልጆች መካከል ፡-
ሀ/ አንዱ 18 ዓመት ሲሞላው የታናሾቹ ሞግዚት በመሆን የቤተሰቡን ይዞታ ተረክቦ የማስተዳደር መብት አለው፡፡
ለ/ ይዞታቸው ከግማሽ ሄክታር በታች ከሆነ በጋራ አርሰው መጠቀም አለባቸው፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5.3 ሐ መሠረት በጋራ አርሰው መጠቀም ካልቻሉ፡-
ሀ/ በጋራ አከራይተው ገንዘቡን ተካፍለው መውሰድ፣
ለ/ አንደኛው ወገን ተከራይቶ የኪራይ ዋጋውን በቅድሚያ ለሌላኛው በመክፈል፣
ሐ/ ለጋራ አራሽ በመስጠት ምርቱን መካፈል፣ ወጪውንም መጋራት፣
መ/ ቀጥሮ በማሳረስ ምርቱን መካፈል፣ ወጪውንም መጋራት፣
ሠ/ ሌላ የአካባቢ አማራጭ ካለ በስምምነት መጠቀም ይቻላል፡፡

5. ማንኛውም አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር ይዞታውን፡-
ሀ/ ለተለያዩ የግብርና አገልግሎት የማዋል፣
ለ/ ቀጥሮ የማሠራት፣
ሐ/ የጋራ እርሻ የማሣረስና
መ/ በማከራየት የመጠቀም መብት አለው፡፡

6. የገጠር መሬትን ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ስለመስጠት፣
1. ለገጠር መሬት ተጠቃሚዎች፡-
ሀ/ ይዞታቸው ተለክቶና ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጣቸዋል፡፡
ለ/ መሬት የመለካቱ ሥራ በዘመናዊ መንገድ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከካርታ ጋር ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፡፡

2. የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርን በተመለከተ፡-
ሀ/ ወጥ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በቢሮው ይዘጋጃል፡፡
ለ/ ደብተሩ የባለይዞታውን ስም፣ የቤተሰብ ብዛት፣ አዋሣኞችን፣ የይዞታውን መጠንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ ይሆናል፡፡

3. የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ለመስጠት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው ፡-
ሀ/ በአንድ ቀበሌ ነዋሪ ሆኖ ይዞታ ያለው አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር ሲሆን፣
ለ/ በአንድ ቀበሌ ነዋሪ ባይሆንም በሌላ አካባቢ ነዋሪ ሆኖ ይዞታ ያለው፣

**3. Among (between) Orphans who lives with legal guardians: -**

**A. When one of the orphans living with the legal guardian aged 18 years, has the right to administer the land being guardian of his younger.**
**B. If their possession is less than half a hectare they should jointly use.**

**4. Not withstanding this article sub article 5.3.(C) if they are unable to use jointly: -**
**A. They can jointly rent and share the money among themselves.**
**B. One of the parties take the land by rent and pay the value early for the other.**
**C. They shall give it for share cropper and share the produce and jointly cover the expense.**
**D. They shall cultivate their land in common with hired labor and share produce among themselves, and jointly cover the expense.**
**E. If there is any local alternative, they shall use it with agreement.**

**5. Any peasant farmer or pastoralist shall have the right to: -**

**A. Use his holding for different agricultural activities.**
**B. Cultivate using hired labor.**
**C. Jointly cultivate with share cropper**
**D. Rent his holding.**

**6. Rural land measurement, Registration and Certification.**

**1. For rural land users: -**
**A. A certificate shall be given for the landholders by measuring and registering their holdings.**

**B. If the land measurement is done using modern technologies, holders shall get a certificate together with a parcel Index map.**

**2. Concerning Land use right certificate: -**
**A. The Bureau shall prepare a uniform rural land use right certificate.**
**B. The rural land use right certificate shall include holder's name, family size, neighbors, area, and other basic data.**

**3. To provide a land use right certificate the following requirements shall be fulfilled: -**

**A. A peasant farmer or pastoralist living in a specific kebele who have a holding.**

**B. Though he is not a dweller in one kebele, he should have holding in other kebele.**

. ሐ/ ይዞታውን በሰፈራ ያገኘ ከሆነ ሕጋዊ የሰፈራ መሥፈርቱን አሟልቶ የተሰጠው፣

4. መሬቱ የባልና ሚስት የጋራ ከሆነ ወይም በሌሎች በጋራ ከተያዘ፡-

ሀ/ ለይዞታቸው የጋራ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጣቸዋል፡፡

ለ/ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ይዞታ ከተጋቡ በኂላ በጋራ አስመዝግበው መጠቀም የሚችሉ ሲሆን የጋራ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርም ይሰጣቸዋል፡፡

ሐ/ ከአንድ ቀበሌ በላይ ይዞታ ያላቸው ባልና ሚስት ወይም ሌሎች ግለሰቦች በየቀበሌው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የማግኘት መብት አላቸው፡፡

5. በከተማ ክልል ለሚኖሩ አርሶ አደሮች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ስለመስጠት፣

ሀ/ በከተማ ክልል ለሚኖሩ አርሶ አደሮች ይዞታቸው ተለክቶና ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲያገኙ የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

ለ/ የሚሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ለሌሎች አርሶ አደሮች ከተሰጠው ጋር ተመሣሣይ መሆን አለበት፡፡

ሐ/ የከተማ ክልል አርሶ አደሮች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የሚያስገኝላቸው ጥቅም የማግኘት መብት ያላቸው ሲሆን የሚጥልባቸውን ግዴታም መወጣት አለባቸው፡፡

6. በሊዝ ወይም በኪራይ የተያዘ የገጠር መሬት፡-
በሊዝ ወይም በኪራይ የሚሰጥ መሬት ከሆነ ተለክቶና ተመዝግቦ አግባብ ባለው አካል ይያዛል፡፡

7. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ፡-

1. በኪራይና በሊዝ መሬት ያገኙ ተጠቃሚዎች፡-

ሀ/ የገጠር መሬት በሊዝ ያገኙ ባለሀብቶች የመጠቀም የጊዜ ገደቡ በሊዝ ህግ መሠረት ይሆናል፡፡

ለ/ የገጠር መሬት በኪራይ ለመጠቀም የገቡት ውል የጊዜ ገደቡ ሳይደርስ የሚፈርስ ከሆነ በውሉ ላይ በተቀመጠው ስምምነት መሠረት ይፈጸማል፡፡

2. የገጠር መሬት ተጠቃሚ፡-

ሀ/ መሬቱ ለህዝብ ጥቅም የሚፈለግ ከሆነ ባለይዞታው የመጠቀም መብቱን ያጣል፡፡

**C. Those who have got land by settlement program, fulfilling the requirements.**

**4. When the land is jointly owned by spouses or any others:**

**A. Both Husband and wife shall jointly get rural land use right certificate.**

**B. If the husband and wife have land holding before their marriage, they shall jointly get a land use right certificate after their marriage.**

**C. Those who have land holdings in more than one kebele, they shall get land use right certificate in each kebeles.**

**5. The provision of land use right certificate for peasant farmers living with in urban territory.**

**A. The Bureau of agriculture and rural development may give delegation to provide a land use right certificate for peasant farmers living with in urban territory.**

**B. The land use right certificate given for peasant farmers in urban territory shall be similar with those who live in rural areas.**

**C. Peasant farmers who are living in urban territory shall get all rights and accept obligations under rural land administration and use proclamation.**

**6. Rural land possessed by lease or rent:-**

**If the land is given through lease or rent it shall be measured and registered by the concerned authority.**

**7. Duration of Rural Land Use right: -**

**1. Users of Leased and rented land : -**

**A. The duration of leased rural land shall be based on the law of the lease.**

**B. If the rent agreement made by the two parties terminates, it shall be done based on the agreement stated.**

**2. Rural land user: -**

**a) The rural landholder shall be evicted from his holding if the land is needed for public purpose.**

ለ/ የመጠቀም መብቱን ያጣው ግለሰብ ተለዋጭ መሬት ያገኛል፡፡

ሐ/ በይዞታው ላይ ላፈራው ሀብትና ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

መ/ የካሣ አከፋፈሉም በሚኒስትሮች ም/ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 135/99 መሠረት ይፈጸማል፡፡

8. በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን ስለማስተላለፍ፣

1. የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች ይዞታቸውን ማከራየት የሚችሉ ሲሆን፡-

ሀ. ማንኛውም አርሶ አደር ወይንም አርብቶ አደር በይዞታው ሥር ያለውን መሬት የቤተሰብ ስምምነት ሲኖር ማከራየት ይችላል፡፡ ስምምነቱም በባልና በሚስት የጋራ ፊርማ ይረጋገጣል፡፡

ለ. ማንኛውም አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር ከይዞ□□ ራሱን በማያፈናቅል ሁኔታ የማከራየት መብት ያለው ሲሆን በ□□ የሚቀረው መሬት የቤተሰቡን ዓመ□ዊ □□ታ የሚሸፍን ምርት የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

ሐ. ሌላ አማራጭ □ለ□ ማለትም ለባለሃብቱ መቀጠር ወይም □ንግድ ሥራ የማካሄድ ወይንም ሌላ አካባቢ ለተሻለ የሥራ ዕድል የመሄድ ፍላጎት ያለው ይዞታውን በሙሉ ማከራየት ይችላል፡፡

መ. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ "ሐ"የተጠቀሰው ጉዳይ የሚያስተዳድረውን ቤተሰብ ችግር ላይ የማይጥል መሆኑ በቤተሰብ አባላት ተረጋግጦ በቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት የስምምነቱ ቅጅ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

2. የመጠቀም መብትን በሚያስተላልፉበት ወቅት፡-

ሀ. የሚከራየው ይዞታ ውሃ ገብ ከሆነ ከመስኖ ልማት ጋር የተያያዙ ግዴታዎችን የመወጣት ኃላፊነት የተከራዩ ይሆናል፡፡

ለ. የኪራይ ውሎች በሁለቱ ተዋዋዮች ስምምነት ካልሆነ በስተቀር ተገቢው ማካካሻ ሳይከፈልና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሳይሠጥ አይፈርስም፡፡

ሐ. ሴቶች፣ አቅመ ደካሞችና ወላጅ አልባ ልጆች ይዞታቸውን በሚያከራዩበት ጊዜ በየደረጃው ከሚገኙ አካላት ጥበቃና ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

መ. የግል ይዞታ በሚከራይበት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በአከራዩ እጅ ይቆያል፡፡

**b. If the Individuals holding is expropriated for public purpose, he shall be given a substitute land.**

**c. He can get compensation for the property and wealth situated on his holding when he is evicted.**

**d. The compensation fee shall be based on compensation regulation No. 135/2007 issued by council of ministers.**

## 8. Transfer of Rural Land Use right

**1. Peasant farmers or pastoralists who got rural land use right certificate shall transfer their possessions when: -**

**A Any peasant farmer or pastoralist can lease out a plot of land under his holding when there is an agreement of his family; the agreement shall be approved by the signature of the husband and wife.**

**B. Any peasant farmer or pastoralist has the right to rent a portion of his holding, which does not evict him totally; the remaining holding should be enough to produce annual food consumption for his family.**

**C. If he has any other alternatives such as working as laborer, being hired by the investor, or to make business or any other better job opportunity, he can rent all of his holding.**

**D. In order to avoid problems related to the provisions in this article, sub article .c, renting should be approved by his family members and the copy of the agreement shall be kept in kebele administration office.**

**2. When land holders transfer their use right:.**

**A. When the landholder rent irrigable land, the rent holder shall be responsible to maintain the obligation related to irrigation.**

**B. Rent contract shall not be terminated unless both parties agree. A party who terminates the contract agreement shall pay compensation to the counter party.**

**C. Special attention shall be given to women and orphans by the concerned body at all level while renting out their holding.**

**D. When private land holding is rented out, the land use right certificate shall be keep with the land holders.**

9. <u>ስለገጠር መሬት ሽግሽግ</u>

1. በዝናብ የሚለማ መሬት ሽግሽግን በተመለከተ፡-

ሀ/ ለግብርና ሥራ ሊውሉ የሚችሉ ያልተያዙ መሬቶች፣ ይዞታ ለሌላቸውና ላነሳቸው አርሶ አደሮች ሊሸጋሸጉ ይችላሉ፡፡

ለ/ በማንም ያልተያዙ የመንግሥት መሬቶች ለአካባቢውና ለክልሉ በሚሰጡት አስተዋጽኦ አንፃር እየተመዘኑ ለአርሶ አደሮች ሊከፋፈሉ፣ ለግል ባለሀብቶችም ሊከራዩ ይችላሉ፡፡

ሐ/ የህዝብ መጨናነቅ ካለባቸው አካባቢዎች በአንፃሩ ወደ ተሻለ አካባቢ በሰፈራ ለሚሄዱ አርሶ አደሮች መሬትን ማከፋፈል ይቻላል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

መ/ ወራሽ የሌላቸው ይዞታዎች፣ ይዞታ ለሌላቸው ወይም ላነሳቸው ሊከፋፈል ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

2. የመስኖ መሬት ሽግሽግን በተመለከተ፣

ሀ/ ከዚህ ደንብ በፊት በመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተዘረጉ የመስኖ አውታር ተጠቃሚዎች ይዞታቸው እንዳለ ይከበርላቸዋል፡፡

ለ/ ከዚህ ደንብ በኋላ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚገነቡ የመስኖ መሬቶች ለኅብረተሰቡ ጠቀሜታ ሲባል ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡

ሐ/ በመስኖ ልማት ምክንያት ይዞታውን ያጣው ግለሰብ፤ በሽግሽጉ የመስኖ ተጠቃሚ ከሆኑት አርሶ አደሮች በዝናብ የሚለማ መሬት በምትኩ ያገኛል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

10. የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች ግዴታ

1. ይዞታውን በእንክካቤ ስለመጠቀም፡-

ሀ/ ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ በሕግ የተሰጠውን መሬት የመንከባከብና የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

ለ/ ተጠቃሚው የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት መልካም አያያዝን በተመለከተ ከኩታ ገጠም ጐረቤቱ ጋር ተባብሮ መሥራት አለበት፡፡

**9. <u>Rural Land Re-allocation</u>**

**1. Concerning rain fed land reallocation:-**

**A) Unoccupied cultivable lands shall be re-allocated for land less and peasant farmers having smaller land size.**

**B) Based on the benefit of the local community and the region in general, unoccupied state land can be re-allocated for farmers or leased for investors.**

**C) When peasant farmers went from densely populated areas to relatively sparsely populated areas by resettlement program, they shall get farmland through reallocation. Details shall be determined by directives.**

**D) Possession with no inheritor can be re-allocated for land less and peasant farmers having smaller land holding. Details shall be determined by directives.**

**2. Re-allocation of Irrigable land.**

**A. Irrigation infrastructures constructed either by government or non-government organizations before the issuance of this regulation shall not be redistributed.**

**B. Irrigation schemes constructed after the issuance of this regulation, either by government or non-government organizations for the betterment of the society, shall be re-allocated.**

**C. Those peasant farmers, who lost a portion of his holding due to reallocation, shall get rain fed land equivalent to what they give. Details shall be determined by directives**

**10. Obligations of Rural Land Users.**

**1. Management of land holding**

**A. Any rural landholder, who got his land legally, is responsible to manage and conserve his holding.**

**B. The land user, regarding land and natural resource management, shall work in collaboration with his neighbor.**

ሐ/ ማንኛውም ተጠቃሚ በመሬት ላይ በደረሰው የተፈጥሮ ሀብት ጉዳትና በመሬቱ ተዳፋትነት ላይ በመመሥረት አፈሩ ተሸርሽሮ ወደ ገደልነት ከተለወጡ ቦታዎች ቢያንስ 10 ሜትር በመራቅ ካልሆነ በስተቀር ማረስ አይፈቅድም፡፡

መ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 10.1 “ሐ” ላይ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የገደሉ መጠን ከ10 ሜትር በላይ ጥልቀት ያለው ከሆነ የጥልቀቱን ርዝመት ያህል ከገደሉ አፋፍ በመራቅ ካልሆነ በስተቀር አርሶ መጠቀም አይፈቀድም፡፡ ሆኖም ደን በማልማት፣ ቋሚ ሰብሎችን በመትከልና ሣር አሣድጎ በማጨድ መጠቀም ይቻላል፡፡

ሠ/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በተከራዩ ላይም ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

2. ማንኛውም ግለሰብ ለመሠረተ ልማት ግንባታ ይዞታውን የመፍቀድ ግዴታ አለበት፡፡ በይዞታው ላይ ላፈራው ሀብት ካሣ የሚከፈል ሲሆን ተተኪ ይዞታም ሊሰጥ ይችላል፡፡ የካሣ አከፋፈሉም በሚኒስትሮች ም/ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 135/99 መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3. የመጠቀም መብት በራስ ፈቃድ ስለመተው፡-

ሀ/ በማንኛውም ጊዜ የመጠቀም መብትን መተው የተጠቃሚው መብት ነው፡፡ ሆኖም ከመጠቀም መብት ጋር ከተያያዙ ግዴታዎች ነፃ መሆን ይችል ዘንድ ተጠቃሚው የመጠቀም መብቱን ለማቋረጥ ከወሰነበት ጊዜ አንድ ወር ቀድሞ መሬትን ለሚያስተዳድር አካል በጽሑፍ ማሣወቅ ይኖርበታል፡፡

ለ/ ማንኛውም የይዞታ መብቱን ያቋረጠ ተጠቃሚ ተሰጥቶት የነበረውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መሬትን ለሚያስተዳድር ሕጋዊ አካል የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

ሐ/ በፈቃዱ የመጠቀም መብቱን ለማቋረጥ የወሰነ ተጠቃሚ በመሬቱ ላይ ያፈራቸውን ንብረቶች የማንሣት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ሆኖም ከይዞታው ተነጥለው መንቀሳቀስ ለማይችሉ ንብረቶች ካሣ የመጠየቅ መብት አይኖረውም፡፡

4. ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተቋማትን በተመለከተ፡-

ሀ/ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተቋማት የልማት ጊዜያቸውን ጨርሰው በሚለቁበት ወቅት አካባበውን ወደነበረበት ሁኔታ የመመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡

ለ/ አካባቢውን ጐድተው የሚወጡ ተቋማትና ግለሰቦች አግባብ ባለው ሕግ ይጠየቃሉ፡፡

**C. Based on the land degradation and presence of gullies caused by natural damages and the slope of the land, any rural land user shall plough his farm at least 10 meters far from gully edges.**

**D. Not withstanding sub-article 10.1'c" in this article, if the depth of the gully exceeds 10 meters plowing shall be forbidden unless the land user leaves a distance equal to the depth of the gully from the gully edges. However, such areas shall be used for forest, perennial crops and grasses.**

**E. All provisions of this article also work on those who have possessed land through rent.**

**2. Any rural landholder shall be obliged to allow his holding for building of infrastructures. Compensation or a substitute land may be given. Compensation fee rate shall be in accordance with the regulation No 135/2007 of the council of ministers.**

**3. When any rural land holder give up his use right in his interest: -**

**A. Any time a rural land user has a right to give up his use right. However, to be free from obligations related to land use right, he shall inform in written application for the concerned body one month ahead..**

**B. Any rural land user who gave up his land use right, shall return his land use right certificate for the concerned body.**

**C. When a land user gave up his land use right in his interest, he shall take the properties he produced on his holding. However he can not claim compensation for the properties that can not be moved.**

**4. Concerning economic and social institutions : -**

**A. When economic and social institutions end up their contract program, they should rehabilitate the environment as to the former conditions.**

**B. Those who left the Environment degraded or polluted shall be asked by the pertinent law..**

5. መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ስለመንከባከብ፡-

ሀ. ለአፈር መሸርሸር በተጋለጡና ተዳፋትነት ባላቸው ቦታዎች የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል ተስማሚ የሆኑ የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን የማከናወንና □ተሠሩ የአፈር □በቃ እርከኖች ካሉም የመንከባከብና የመጠገን □ጸ ታ አለበት፡፡

ለ. ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በተከራየው መሬት ላይ ቢያንስ 10% ለአካባቢ ተስማሚ □ሆኑ ሁለገብ ጠቀሜታ ያላቸውን □□□ ዝርያ መትከል አለበት፡፡

ሐ. ማንኛ□ም ግለሰብ ወይም ድርጅት የኪራይ ውል ዘመን ሲያበቃ ወይም ውሉ ሲቋረጥ የመሬቱ የተፈጥሮ ይዘት እንደተጠበቀ ለአከራዩ በወቅቱ የማስረከብ □ጸ ታ አለበት፡፡

11. የገጠር መሬት አነስተኛ ወለልና ኩታ ገጠም ይዞታን በተመለከተ፣

1. የገጠር መሬት አነስተኛ ወለልን በተመለከተ፡-

ሀ/ ማንኛውም አርሶ አደርና አርብቶ አደር ይዞታውን ለቤተሰቡ አባል በውርስ የማስተላለፍ መብት ያለው ቢሆንም ይዞታው ከተወሰነው ዝቅተኛ መጠን በታች ከሆነ ወራሾች በጋራ መጠቀም አለባቸው፡፡

ለ/ ባልና ሚስት በሚፋቱበት ወቅት የእያንዳንዳቸው ድርሻ ከአነስተኛ ወለል በታች ከሆነ ከመከፋፈል ውጪ በሌላ አማራጭ መጠቀም አለባቸው፡፡

ሐ/ በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1-ሀ ከተወሰነው የማሣ መጠን በታች ከሆነ ተጠቃሚዎች ከመከፋፈል ውጪ በሌላ አማራጭ መጠቀም አለባቸው፡፡

መ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 11.1 ከሀ-ሐ በተጠቀሰው መሠረት መጠቀም ካልተቻለ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 ከሀ-ሠ በተደነገገው አማራጭ መጠቀም ይችላሉ፡፡

2. የኩታ ገጠም ማሳዎች ልውውጥን በተመለከተ፡-

ሀ/ በባለይዞታዎች ፈቃድ የይዞታ ልውውጥ በሚደረግበት ጊዜ የመሬቱ ስፋት፣ የለምነት ደረጃ፣ ለአደጋ ተጋላጭነትና የመሣሠሉት ግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡

ለ/ የይዞታ ልውውጡ ከመጽደቁ በፊት ለባለጉዳዮች ውሣኔያቸውን በጥንቃቄ እንዲያዩ የአንድ ወር ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡

ሐ/ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባለጉዳዮች በይዞታ ልውውጡ ከተስማሙ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይቀየርላቸዋል፡፡

**5. Managing Land and Natural Resources**

**A. Any rural land user has the obligation to implement appropriate soil and water conservation methods on land and other natural resources and maintains structures.**

**B. Any individual or organization, who got land by rent or lease, has to plant at least 10% multi-purpose trees.**

**C. When the contract period comes to an end or in case the contract agreement terminates, the investor is supposed to hand over the land to landholder without endangering natural resources bases.**

**11. Determining the minimum rural land holding size and encouraging land consolidation**

**1. The smallest size of rural land**

**A. Any peasant farmer and pastoralist have the right to inherit his possession for his family members; however, if the size of the land is less than the minimum, they have to use their land jointly.**

**B. When possession of the divorced spouses is less than the size of the minimum holding, and therefore they shall use the land jointly by any means other than sub-division.**

**C. If the size is less than the minimum size determined on provision of article 11 sub-article 1.A of the proclamation, landholder can use it other than sub-division.**

**D. On this article, sub-article 11.1A-C, if the holders can not use it on the basis of the given choices, they can use it on the provision of this regulation article 5 sub-4A-E**

**2. Exchange of adjacent holding**

**A. When land holding exchange on voluntary basis is done between holders, size of the holding, fertility status, and vulnerability for damage … etc shall be taken in to consideration.**

**B. Before the approval of land exchange, one month shall be given to both parties to carefully see their decision.**

**C. If the two parties agreed on exchange of their holding, they shall get a new land use right certificate within a month.**

3. የመሬት ልውውጡን ሌላው ኅብረተሰብ እንዲያውቀው ፡-

ሀ/ ለአንድ ወር ያህል በቀበሌው አስተዳዳር አማካኝነት ማስታወቂያው በግልጽ ቦታ ተለጥፎ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

ለ/ በተጨማሪም በአካባቢው በተለመደው የመልዕክት ማስተላልፊያ ዘዴ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

## 12. የክርክሮች አወሣሠን፡-

ማንኛውም ከገጠር መሬት ይዞታ ጋር የተያያዘ ክርክር፡-

ሀ/ ጉዳዩን ሽማግሌዎች በዕርቅ ከጨረሱ ስምምነቱ ለሁለቱም ወገኖች በጽሁፍ መሰጠት አለበት፡፡

ለ/ ጉዳዩ በሽማግሌዎች በዕርቅ ካልተፈታ ለሁለቱም ወገኖች ያልተስማሙበት ሁኔታ በጽሁፍ መሰጠት አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

### በገጠር መሬት አጠቃቀም ረገድ ስለተጣሉ ገደቦች፡-

13. የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ስለማውጣትና ስለተዳፋት ቦረቦርና ረግረጋማ መሬቶች አጠቃቀም፣

1. ስለተዳፋት መሬቶች አጠቃቀም፡-

ሀ/ ሜዳማ በሆኑ መሬቶች ላይ (0-2%) የጥንፋፎ ሥራዎች ካሉ በማከናወን መጠቀም አለባቸው፡፡

ለ/ ከሜዳማነት እስከወጣ ገባ ባሉ ሰበርባራ መሬቶች ላይ (3-10%) ተገቢ የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን በማከናወን ለተለያዩ የእርሻ ተግባራት መጠቀም ይቻላል፡፡ ለዚህ ተዳፋትነት የሚያስፈልጉ የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን ሳያከናውኑ መጠቀም አይፈቀድም፡፡

ሐ/ ተዳፋት የሆኑ መሬቶች (11-15%) ማለትም ጥልቅ አፈር የሌላቸው፣ አነስተኛ ለምነት ያላቸው፣ ለአፈር ክለት የተጋለጡና ለረድፍ /መሥመር/ ሰብሎች የማይመቹ መሬቶች ስለሆኑ የተመረጡ የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን ሳያከናወኑ ዓመታዊ ሰብሎችን መዝራት ወይም መትከል አይፈቀድም፡፡

መ/ በጣም ተዳፋት የሆኑ መሬቶች (15-30%) ማለትም ጥልቅ አፈር የሌላቸው፣ ለም ያልሆኑ፣ ለክለት የተጋለጡ፤ ቦረቦር መሬቶችን ለዓመታዊና ለረድፍ ሰብሎች መጠቀም አይፈቀድም፡፡ ሆኖም ተገቢ የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን በመሥራት መጠቀም ይቻላል፡፡

**3. To make aware of community about land exchange:-**

**A. When holders exchange their holdings, the kebele administration shall stamp the notice on an open place for a month.**

**B. In addition, it must be announced for the community by using the known traditional ways of communications.**

## 12. Dispute resolution

**The disputes in relation to any rural land shall be determined: -**

**A. If the two parties settle their problem using local elder reconciliation, the agreement shall be give to both parties in a written letter.**

**B. If the dispute is not settled by the arbitration of local elders, both parties hall get written letter describing the reason why the two parties disagree.**

## Section Three

### Restrictions Imposed on Rural Land Use

## 13. Land Use Planning and Proper Use of Sloppy, gully and wetlands.

**1. About Sloppy lands**

**A. Plain areas having 0-2% slopes can be used for agriculture by draining if necessary.**

**B. On lands having level to undulating slope (3-10%), the landholder shall cultivate using appropriate soil and water conservation measures. It is not allowed to cultivate such lands with out applying appropriate measures.**

**C. On lands having 11-15% slope with shallow soil depth, low soil fertility and exposed for erosion, since such lands are not suitable for row cropping, implementation of appropriate soil conservation techniques is a must. Therefore, it is forbidden to plant annual crops without applying appropriate conservation measures.**

**D. On steep slopes, having 15-30% slope, with shallow soil depth, low soil fertility, and being exposed for erosion are not allowed for annual and row crops. However, it is possible by applying appropriate soil conservation measures.**

2. ስለረግረጋማ መሬቶች አጠቃቀም፡-

ሀ/ ረግረጋማ መሬቶች በደለል እንዳይሞሉና በውስጣቸው ያሉት ብዝሃ ህይወቶች እንዳይጠፉ በጥናት በተደገፈና ኅብረተሰብን ባሳተፈ መልኩ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

ለ/ ለእርሻና ለሌሎች ሥራዎች ረግረጋማ መሬቶችን ማጠንፈፍ ክልክል ነው፡፡ ሆኖም የአጠቃቀም ዕቅድ ወጥቶላቸው መጠቀም ይቻላል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

3. ለህዝብ ጥቅም ሲባል ስለሚለቀቅ መሬት፡-

ሀ/ ለክልሉ ልማትና ለአካባቢው ዕድገት የተሻለ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የታመነበት ኘሮጀክት ሲቀረጽ ባለይዞታው ተገቢ ካሳና ተተኪ ይዞታ ተሰጥቶት መሬቱን እንዲለቅ ይደረጋል፡፡

ለ/ ተተኪ ይዞታ መስጠት በማይቻልበት ጊዜ ባለይዞታው ወደፊት ህይወቱን መምራት የሚያስችለውን የገቢ ማስገኛ/መተዳደሪያ/ በኘሮጀክቱ ተጠቃሚዎችና መሬቱን ለልማት በጠየቀው ድርጅት ምክክር እንዲዘጋጅለት ይደረጋል፡፡

ሐ/ ለልማት ሲባል ለሚለቀቅ ይዞታ ካሳ በቅድሚያ የሚከፈል ሲሆን ክፍያው ከተጠናቀቀ በኂላ በሶስት ወር ውስጥ ይዞታውን የመልቀቅ ግዴታ አለበት፡፡

መ/ ባለይዞታው ማሣ ላይ ያለ ዓመታዊ ሰብሉን ለማንሣት ጊዜ ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም የልማት ኘሮጀክቱ ጊዜ የማይሰጥ ሁኔታ ውስጥ ሲሆን ለሰብሉ ካሣ ተከፍሎ የኘሮጀክቱ ሥራ ይጀመራል፡፡

**2. About the Use of Wet lands.**

**A. Wet lands, based on a study and with community participation, shall be protected from sedimentation and loss of biodiversity. Details shall be determined by directives.**

**B. It is forbidden to drain wetlands for farming and other purposes. However, they can be used based on study and supported by local development plan. Details shall be determined by directives.**

**3. Expropriation of Rural Lands for public purpose**

**A. When a project is prepared for the development of the region and local community, the land holder shall be obliged to give up his holding after getting a substitute land.**

**B. When it is impossible to get substitute land, an income generation means will be devised with discussion between the beneficiaries and owner of the project to sustainably lead holder's livelihood.**

**C. When the land holder is expropriated due to development activities a compensation shall be paid in advance. Then the land holder is obliged to leave the land with in three months.**

**D. A time shall be given for the holder to harvest his annual crop. However, if the project is sensitive, it can be started after paying compensation for the landholder.**

4. መሬትን በአግባቡ ካለመያዝ የተነሳ የመጠቀም መብትን ስለማጣት:-

ሀ/ በመሬቱ ላይ ተገቢ የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን ባለመሥራቱ አፈሩ ከተከላ፡ ለአካባቢው ተስማሚ የሆኑ ዛፎችን ባለመትከሉ አካባቢው ከተራቆተና አግባብ ያለው አካል አካባቢው ከአያያዝ ጉድለት የተነሣ መጐዳቱ በመረጃ ተደግፎ ሲቀርብ የመጠቀም መብቱን ያጣል፡፡

ለ/ ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ የመጠቀም መብቱን ከማጣቱ በፊት በየደረጃው ከሚገኙ የቀበሌ አስተዳደርና የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ከስህተቱ እንዲታረም መጀመሪያ የቃልና ሁለት ጊዜ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያዎች በየወቅቶቹ እንዲደርሱት ይደረጋል፡፡

ሐ/ ማስጠንቀቂያ ሰጪው ህጋዊ አካልም በአድራሻ ለመሬት ተጠቃሚ ሲጽፍ በግልባጩ የበላይ አካሉን አሣውቆ ስምምነት ሲያገኝ የመጠቀም መብቱን እንዲያጣ ይደረጋል፡፡

መ/ በመሬቱ የመጠቀም መብቱ እንዲቋረጥ የተወሰነበት ባለይዞታ ውሣኔው በተገለጸበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ለሚመለከተው አካል የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

ሠ/ የመጠቀም መብቱን እንዲያጣ የተወሰነበት ግለሰብ ባቀረበው ቅሬታ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ካልተሰጠ በስተቀር ለአዲስ ተጠቃሚዎች ቋሚ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አይሰጥም፡፡

5. ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ መሬቱን ከሁለት ተከታታይ ዓመታት በላይ ጾም ማሳደር የለበትም፡፡ ፆም ማሣደሩን የቀበሌ አመራር ካረጋገጠ በኂላ የመሬት አስተዳደር ኮሚቴና የአካባቢ ሽማግሌዎች ይዞ የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ ከስድስት ወር በኂላም ካልታረሰ ለተጨማሪ ስድስት ወራት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ በዚህ ማስጠንቀቂያ መሠረት ካልተፈጸመ የመጠቀም መብቱን ያጣል፡፡ ሆኖም:-

ሀ/ በመታመሙ ወይም በህግ በመታሰሩ፣
ለ/ በቤተሰቡ የሞት አደጋ ደርሶ የሚያርስ ከጠፋ፣
ሐ/ በድርቅ፣ በውሃ መጥለቅለቅና በሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች፣
መ/ ሌሎች በቀበሌው አስተዳደር የታመኑና ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች መኖራቸው ሲረጋገጥ የመጠቀም መብቱን አያጣም፡፡

6. የወል መሬቶች አጠቃቀም:-

ሀ/ በወል ይዞታነት የሚታወቁ ጉብታዎች የተራቆቱና ምርታማ ያልሆኑ መሬቶች በቀላሉ ሊጐዱ የሚችሉ ተዳፋትና ተራራማ አካባቢዎች በአግባቡ ለመጠቀም በኅብረተሰቡ ተሳትፎ በግል ወይም በጋራ የሚለሙበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡

**4. Termination of Land Use Right because of miss-use.**

**A.** **An-individual shall loose land use right when he fails to implement soil conservation techniques, and leave the soil to erode, when he does not plant trees suitable to the environment, and the concerned official states the problem with evidence.**

**B.** **Any rural land user, before he looses his possession, he has to get warning first orally and then twice in the form of letter from kebele Administration & wereda agriculture and rural administration office.**

**C.** **When the concerned legal body writes a letter of land use right termination after notifying it to the higher body, then the landholder obliged to be evicted.**

**D.** **Any land user who is evicted from his possession, he is obliged to return the land use right certificate with in a month after the decision.**

**E.** **The new land user can not get a land use right certificate unless the last decision is made on the reconsideration claimed by the looser.**

**5. Any rural land user shall not negligently let fallow his land more than two consecutive years. After the kebele administration approves the land is not ploughed it shall give oral warning with kebele land administration & use committee together with local elders. Then, if it is not ploughed after six months, the kebele administration shall give written warning for the next six months. Still, if it is not done based on the warning, he shall loose his use right. How ever, when:-**

**A.** **He is sick or put in prison,**
**B.** **There is no land tiller due to death of his family member.**
**C.** **Drought, flooding, and other natural calamities occur, and**
**D.** **Rural land user faces problems and accepted by the kebele administration, he shall not loose his land use right.**

**6. Communal Land use.**

**A.** **With the participation of the community, efforts shall be made in order to utilize properly communal lands such as undulating,, bare, un productive, sloppy and hilly areas, which can be easily damaged, either privately or jointly.**

ለ/ የወል መሬቶች በአካባቢው ኅብረተሰብ ተሳትፎና በሚመለከተው መ/ቤት ምክክር ወደ ግል ይዞታ ተቀይረው ለደን፣ ለግጦሽና ለቋሚ ተክል ልማት ይውላሉ። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

ሐ/ የወል መሬቶች ለዓመታዊ ወይም ለቋሚ ሰብል ልማት ለግለሰቦች አይከፋፈሉም። ሆኖም በአካባቢው የእርሻ መሬት እጥረት መኖሩ ሲታመን፣ የመሬቱ ተዳፋትነት ለዓመታዊ ሰብል የሚፈቅድ መሆኑ ሲታወቅና ተጠቃሚው ማህበረሰብ በጉዳዩ አምኖበት በ2/3 ድምጽ ሲወሰን ብቻ ሊከፋፈሉ ይችላሉ።

መ/ መሬት አልባ ወጣቶች ወይም መሬት ያነሣቸው አርሶ አደሮች በማህበር ተደራጅተው የወል መሬቶችን በጋራ ለመጠቀም ጥያቄ ሲያቀርቡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ሐ መሠረት ይፈጸማል።

ሠ/ የወል መሬት የይዞታ ለውጥ ከተከናወነ በኂላ ሁሉም ለውጡ የሚመለከታቸው ተጠቃሚዎች ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማውጣት ይችላሉ።

B. With the participation of the local community and the concerned government body consultations, communal lands shall be transferred to private ownership so as to utilize them for forestry, grazing and perennial crops. Details shall be determined by the directives.

C. Communal lands shall not be transferred to private ownership for the purpose of growing annual crops. However in areas where there is farmland scarcity, it is possible to transfer by considering the slope of the land and its suitability for annual crops when it is decided to reallocate by two third of the local community.

D. When land less youths or peasant farmers who have less land claim for land in association, it shall be done on the basis of this article sub article 'c'.

E. Right after land holding change occur, the landholders shall take a land use right certificate within a month.

7. የመንግስት ደን መሬቶች አጠቃቀምን በተመለከተ፡-

ሀ/ በመንግሥት ደን ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮች በደኑ ውስጥ የሚገኙ እንጨት ያልሆኑ የደን ውስጥ ሀብቶችን ማለትም የጫካ ቡና፣ ኮረሪማ፣ እጣን፣ ሙጫና ሌሎችን የመጠቀም መብት አላቸው።

ለ/ በደኑ ዙሪያ ላሉ አርሶ አደሮች ከደን ውጭ ያለ ይዞታቸው ተለክቶ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጣቸዋል።

ሐ/ በማንኛውም ሁኔታ በመንግሥት የተያዙ የደን መሬቶች ተለክተው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ለግለሰቦች ወይም ለድርጅቶች አይሰጥም።

7. About Government forest land use

A. The local community found around state forest, has the right to use non-timber forest products (forest coffee, cardamom, incenses, gum, etc) from state forest.

B. Peasant farmers living on the surrounding of state forest, land use right certificate shall be given by measuring and registering their holdings out side the state forest.

C. State forestlands, by any condition, shall not be measured, and registered so as to give land use right certificate for individuals or organizations.

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ኃላፊነት

ሀ/ በየቀበሌው ከ5-7 አባላት ያሉበት የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴን በህዝብ ያስመርጣል።

ለ/ የኮሚቴው ተግባር፤ ኃላፊነትና የሥራ ዘመን በመመሪያ ይወሰናል።

## Section Four
## Miscellaneous Provisions

14. Responsibility of the Regional Bureau of Agriculture and Rural Development

a/ The bureau shall let the community to elect about 5-7 rural land administration and use committee member in each kebele,

b/ The duties, responsibilities and duration of committee shall be determined by the directives.

15. የመተባበር ግዴታ
ማንኛውም አካል ይህን ደንብና ደንቡን ተከትለው የሚወጡትን የአፈፃፀም መመሪያዎች ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

16. ስለ ቅጣት፡-
ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ወይም ደንቡን ተከትለው የሚወጡ መመሪያዎችን ጥሶ ሲገኝ አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡

17. ስለተሻሩና ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጐች፣

ሀ/ ከዚህ ደንብ በፊት በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 16/1996 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

ለ/ ከዚህ ደንብ ጋር የሚጋጭ ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በደንቡ የተካተቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

18. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፡-
የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ለዚህ ደንብ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡

19. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ፣

ሀ/ በክርክር ላይ ያሉ ጉዳዮች (ውሣኔ ያላገኙ ጉዳዮች) በሙሉ በአዋጅ ቁጥር 110/99 እና በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

ለ/ ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር 53/95 እና በደንብ ቁጥር 16/96 መሠረት በየደረጃው በይግባኝ፣ በሰበርና በአፈፃፀም ላይ ያሉ የመሬት ክርክር ጉዳዮች በዚያው ፍ/ቤት በቀድሞው አዋጅና ደንብ መሠረት ውሣኔ ያገኛሉ፡፡

20. ደንቡን ስለማሻሻል
የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህን ደንብ ማሻሻል ይችላል፡፡

21. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ
ይህ ደንብ ከዛሬ ታህሳስ 14 ቀን/2000 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሽፈራው ሽጉጤ
የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች
ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር

**15. Obligations to cooperate**

**Any individual/organization is responsible to cooperate in implementing the provisions in this regulation and directives which will be issued following this regulation.**

**16. About penalty**

**Where any individual is found violating provisions in this regulation and directives issued following this regulation, he shall be penalized in accordance with the pertinent law.**

**17. About Repealed and Inapplicable laws.**

**a/ Regulation No. 16/2004 issued by the regional administrative council is repealed here after.**

**b/ Any regulation, directive or customary practice that contradicts with this regulation shall not be applicable.**

**18. Mandate for issuing directives**

**Bureau of Agriculture and Rural development shall have the power to issue directives.**

**19. Transitory provisions**

**a/ All land holding dispute cases under arbitration (not decided) shall be resolved in accordance with proclamation No. 110/2007 and this regulation.**

**b/ Land holding dispute cases, at all levels under appeal, cassation and implementation phases that are being treated based on proclamation No 53/2003 and regulation No. 16/2004 shall be resolved by the concerned court in accordance with previous proclamation and regulation.**

**20. Amendment of the Regulation.**

**Where necessary, the regional administrative council shall amend this regulation.**

**21. Effective Date**

**This regulation shall enter in to force on this December 24 date of 2007**

**SHIFERAW SHIGUTE**
**President of the Regional state of Southern Nations, Nationalities and Peoples**